# ስርአቱን ወይስ መሪውን?

ሲራክ ከሚድ ዌስት

ላለፉት በርካታ ቀናት ስለ አገራችን ጠቅላይ ሚኒስትር መታመም ሳንጠግብ በመሞታቸውና ባለመሞታቸው ስንመራመር እንገኛለን። ያለመሞታቸውን የሚመኙ ባንድ እገር ቆመው የሚጸልዩትን ያህል መሞታቸውን የሚመኙ ደግሞ ካንድ እግር ያነስ ነገር ቢኖር በዚያም እንደሚጸልዩ አጠያያቂ አይሆንም። መቼም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞተውም ሆነ ታመው ለደገፉአቸው ወሮታ ለመክፈል የሚያስቡትን ያህል የገደሉአቸውን ደግሞ እኔን አያድርገኝ እየዛቱ ስለመሆናቸው መገመት አያስቸግርም።

ሁሉም ባንድ እውነት ላይ የሚስማማ ይመስላ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመታመማቸው። ሰው ስይታመምም ሊሞት ቢችልም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሞቱ ታመው ነው የሚለው ይበረክታል አንዳንዱ ስይታመሙ ሞቱ ቢልም። ብዙ ሕዝብ አሳምመው ገድለዋልና ይህን ለሳቸው የሚመኙ ደግሞ ቢያንስባቸው እንጂ አይኀላባቸውም። ህመማቸው ባይታወቅም ያእምሮ በሽታ፡ ያንጀት ካንሰር፡ የደም ካንሰር፡ የስራ መብዛት ካንሰር፡ የስልጣን ካንሰር . . . . ያበበው ገላ ጨኸት . . . እንዲያው ባንዱ ወይም በሁሉም በሽታ ተለክፈዋል ብለን እንተማመን ባንድ ህመም መሞትና በዘጠና ዘጠኝ በሽታም መሞት ያው ሁሉም ሞት አንድ ሞት ነው። ግን ቢሞቱም ገና በበሽታቸው አልተስማማንም። በመሞታቸውም ሕዝቡ ቀርቶ ጋዜጠኛውም ገና መስማማት አልጀመረም። እናም በሽታቸው፡ አማማታቸውና አቀባበራቸው ገና እንቆቅልሽ ሊሆን ይሆን?

የጋዳፊን መሞት፡ የኦሳማን መሞትና የለሎቹንም አምባገነን ገዢዎችን አወዳደቅ የዘገቡ ታላላቅ የዜና ድርጅቶች ምነው የኚህን ጠቅላይ ሚኒስቴር በሽታ ሚስጢር ቢሆንባችውም ሞታቸውን ማርዳት አቃታቸው? ያሜሪካን መንግስት ዜናውን እንዳይዘግቡ ስላላቸው ነው የሚሉ ሰዎች ቁጥር ብዙ ነው። ብዙ ስለሆኑ ግን እውነት ነው ማለት አይቻልም። እንዲህ አይነቱ እምነት ደግሞ ቢቢሲንና የወያኔን ዜና ማሰራጫዎች አንድ ማድረግ ይሆናል።

የተቃዋሚው ጎራ ሁሉ እንዲወያይ አጀንዳ ሰጭው ወያኔ ነው የሚባለው ነገር እውነትነቱ እየጎላ ይታያል። አሁንማ ለአጀንዳው አቀራረጽ የሚረዳው ከሆነ ወያኔ የመሪውንም ህልውና እስከመግደል እንደሚዘልቅ የሰሞኑ ልብ ሰላቢ ወሬ ማስረጃ አይሆንምን? ስለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሽታ ስንመራመር ከረምን። አሁን ደግሞ ሞተዋልን አልፈን አስከሬናቸው ሃገር ገባ የለም በብራሲልስ ነው ያለው ከሚል የማይረባ ክርክር ገብተናል። ሌላው ደግሞ ሞቱን አንናገርም ያሉት ወያኔዎች ናቸው ይሉናል። እውነትነቱ ቢጎላም እስከመቼ? እንደ ሰባት አመት ባጽም መገዛት አይነት ይሆን? ታዲያ እንዴት አድርጎ ስባት አመትና አርባ ቀናት ይቀራረባሉ?

በጠቅላይ ሚኒስትሩ መታመም/አለመታመም ወይም መሞት/አለመሞት ስንክራከር ወያኔዎቹ ጉልበታቸውን እያጠናከሩ ስለመሆናቸው ዘንግተናል። ከጠቅላይ ሚኒስትሩ መታመምና መሞት በላይ የላቁ ቁም ነገሮች በኢትዮጵያ እየተካሄደ ነው ያለው። እስላሙ ወገናችን ለመብቱ እየተዋደቀ ይገኛል። ክርስቲያኑ ወገናችን የህልውና ትግሉን ተያይዞታል። መምህሩና ተማሪው የጀግንነት ታሪኩን በማደስ ወገኑን እያነቃቃ ይገኛል።ላብ አደሩና ገበሬው የድህነትና የባርነት ቀንበሩን በጣጥሶ በድል ለመወጣት መራራውን ትግሉን ተያይዞታል። እንደ ሳሙና እየመነመነ ያለውን ያገራችንን መሬት ከባእዳን እጅ ፈልቅቆ ለማውጣትና አገርን ለማዳን ሕዝቡ በየአካባቢው ደሙን እያፈሰስ አለ። ይህን የተለያየ ትግል ማቀናጀት ይገባል። አንድም ይሁን ብዙ ድርጅቶች የሕዝቡን ትግል ለማቀናጀት መነሳሳት ከሚጠይቅ ፈታኝ ወቅት ላይ ደርሰናል ሊቀመንበሩ አሉ የሉም ከሚል  ከእንቁላል ወይስ ጫጩት ክርክር መጣት አለብን።

እንዲህ አድርገን ነገሩን እንዝጋው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዛሬ ሞተዋል እንበል። ሞቱ ማለት ከስራ ገበታቸው ተለዩ ማለት ብለን ብንውስድም ከስራ ገበታ መለየት ግን ሁሌም ሞት ነው ከሚል ግብዝነት እንዳንዘፈቅ መጠንቀቅ አለብን። ግን መስራት አይችሉም ምክንያቱም ሞተዋልና ብለን ራሳችንን እናሳምን። አርባ ቀናት ከስራ ገበታቸው ተለይተዋል። እና የዛሬ አርባ ቀናት ገደማ መሞትና ዛሬ መሞት ሁሉቱም ሞት አይደሉም እንዴ? እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሞቱ ስንብተዋል እንበል። ስለሞቱ ወያኔ መግዛቱን ተነጠቀ እንዴ? ይህን ጥያቄ ሳልመልስ ወይም እናንተ ሳትመልሱት ወደ ክፍል ሁለት ልዝለቅ።

ጉዳዩ ጉልቻን ቀይሮ ወጥን አጣፍጣለሁ መባል ጋር ይመሳሰላል። ወጡን እንደ ስርአት ከወሰድነው መለስ ጉልቻ ነው የሚሆነው። መለስን በስዩ በአቦ ጸሃዬ በበረከት በሃይለማሪያም . . . ወይም በጫልቱ  መተካት ይቻላል ብለውናል አንድ

አንጋፋ ወያኔ። ስርአቱንስ መለወጥ እንደ መለስን  መለወጥ ቀላል ነውን? እንዲያው አጻጻፌን ላሳምር ብዬ እንጂ መልሱ ሳታልሙት የታወቀ ነው። እኔማ የራሴን ጥያቄ ሳልጨርሰው መልሱን አውቄዋለሁ ጉራ ባይሆንብኝ። ወገኖቼ እንዲያው ለመድከም ያህል ዙሪያውን ዞርኩት እንጅ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞቱ አልሞቱ ወያኔ መግዛቱ አይቀሬ ነው ወገባችንን አስረን መታገል ካቃተን። ደግሞ ደጋግሞ መሰመር ያለበት ሃቅ ደግሞ ወያኔን ዲያስፖራ ሜዳ ላይ ሆነን አንጥለውም። በርግጥ የዲያስፖራው ትግል አያግዝም አልተባለም። የዲፕሎማሲ ስራ በሚገባ መስራት ይችላል። አገር ቤት ላለው ትግል የገንዘብ ጉልበት ማሰባስብ ይቻላል። ከህዝብ የሰበሰብነውን ገንዘብ እንደ አይጥ መብላት ካልለመደብን በስተቀር።

አሁንም ወደ ዋነኛው ጥያቄ ወይም መሰረታዊ ወደ ሆነው ጉዳይ ልመለስና ስርአቱን ወይስ መሪውን ነው መፈንገል የሚጠበቅብን? አንድ ሳር ቢመዘዝ ጎጆ አያፈስም። ወይም ጎጆው አይፈርስም። ወይም ጠቅላይ ሚኒስትሩን እንደ ቤት ጉልላት ብንወስዳቸውና ጉልላቱን ብንጎምደው ቤቱ አይገረሰስም። ቤቱን እንደ ስርአት ከወሰድነው ጉሉላቱ ሲናድ ቤቱ እንዳልተናደ ሁሉ ሰርአቱም አይናጋም። ቤቱን ለመናድ መሰረቱን መነቃቀል አለብን። ስርአቱንም ጠራርጉ ለመቀየር አብዮት ማካሄድ የግድ ይላል። በወያኔ ስርአት ላይ መሪውን ቀይሮ ለመኮፈስ ማሰብ እንደ ወያኔ መግማማት ከመሆን አያድንም። ወደ ስልጣን ለመውጣት ቅርብ መንገድ የሚምኙ እንደ የሽግግር ሽንጎ ፈጣሪዎች ወይም መፈንቅለ መንግስት ሕልመኞች ህልማችሁ የቀን ቅዥት ነው ሊባሉ ይገባል። ዋንኛውን ትግላችንን ትተን በወያኔ ጎራ ያለውን ትርምስ በማዳነቅ ም/ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን የሚያስይዝ ህግ የላቸውም፡ አዜብ ካገር እንዳትወጣ ታገደች (ግን የነበረችው እኮ አውሮፓ ነበር ስትከለከል)። ያሜሪካን መንግስት ስዬን ብርቱካንን ብርሃኑን . . . ነው ማስቀመጥ የሚፈልገው የሚለው መላምት ባይናቅም ባንድ ጊዜ ግን ሶስት ጠቅላይ ሚኒስቴር ማስቀመጥ ይቻል ይሆን? ያሜሪካ መንግስት ፍላጎቱ መጥፎውን ጠቅላይ ሚኒስትር በሌላ መጥፎ ለመተካት ከሆነ ፍላጎቱ የኢትዮጵያ ሕዝብን ፍላጎት አላወቀም ማለት ነው። እንዲያው ለነገሩ ስንት ዘመን ይፈጅብን ይሆን አሜሪካ ለኢትዮጵያ የሚበጅ መንግስት ታመጣለች የሚለውን ምኞታችንን ለመቀየር? ጉዳዩ እኮ ኢትዮጵያ እጆቹአን ወደ አሜሪካ ትዘረጋለች ሆነ ማለት ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞቱም አሉ መንግስታቸው ባዶ መንበራቸውን ይዞ ያለሳቸው ይሄው ላለፉት አርባ ሁለት ቀናት እየገዛ ነው። ይህ ደግሞ ተጠቃለው ቢቀበሩም ጉዞው ይህን እንደሚመስል ያመላክታል። ምናልባት በመሞትና በመቀበር መካከል መከራከር እስካልጀመርን ድረስ። ለኔ ሞተ ተቀበረ ነው ተቀበረም ሞተ ነው። የቃላት ምርጫ ካልሆነ በስተቀር። እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ የወያኔን ስርአት ለማስቀጠል የማይሞቱ (ፍጹማዊ) መሆን የለባቸውም። እንደሰው ያልፋሉ። ሲያልፉ (በክፉም ይሁን በበጎ) ወያኔ ቦታቸውን የሚተካ የበለጠ አምባገነን መሪ ድሃ አይደለምና ይተካቸውና ስርአቱን ያራምዳል። እንዲህ እንዳይሆን የሕዝቡ ትግል አምርሮ የወያኔን ስርአት መነቃቅሮ መጣል አለበት። ያንንም ለማድረግ አማራጩ ጊዜያዊ የሽግር ሽንጎ መመስረት አይደለም። ወይም አሜሪካንን መለመን አይደለም። ወይም ጥርስ የሌለው ሕብረት፡ጥርቅም፡ ቅንብር፡ ቅንጅት፡ ጥምረት፡ መድረክ፡ አማራጭ ሃይሎች ... አይነት የቃላት ጫጫታ ፖለቲካ ነጻ ሊያወጣን ቀርቶ ከዲያስፖራው መድረክ ፈቅም አያደርገንም። ወይም የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ቂላ ቂልነት ይዘን ኢትዮጵያን ነጻ ለማውጣት አስመራ ምሽግ ማድረግ አይጠበቅብንም። ለነገሩማ የጠላቴ ጠላት ጠላቴም ሊሆን ይችላል እኮ።

አረጋዊ ወያኔ እንዳሉት መለስ ቢሞት የወያኔ ስርአት ያከትማል ማለት አይደለም። ወያኔ እንደ መለስ የሚገዛን ጨካኝና አምባገነን ጠቅላይ ሚኒስትር መተካት አይሳነውም። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪው በቃ ሳይሆን ታገል ታገል ታገል ይሁን!!!